# ኤሌክትሮኒክስን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል

ኤሌክትሮኒክስን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የተፈጥሮ ሃብቶችን ይቆጥባል፣ መርዛማ ንጥረ ነገሮችን በ አ ግባቡእንደተያዙ ያረጋግጣል፣ ይበልጥ የሚቆዩ የከበሩ ማዕድናት ሃብትን ይሰጣል፣ እናም የሰው ልጅን ጤና እና አካባቢ ይጠብቃል።

## eCYCLE DC

በዲስትሪክቱ ውስጥ የተሸጡ የአንዳንድ ኤሌክትሮኒክ እቃ አምራቾች በከተማ ውስጥ የሚፈጠረውን የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ እንደገና ጥቅም ላይ ለማዋል በዲስትሪክቱ ውስጥ ላሉ ሰዎች መስጠት አለባቸው። DOEE ይህንን ፕሮግራም ይቆጣጠራል።

ለበለጠ መረጃ እባክዎ ከዚህ በታች ያለውን ማስፈንጠሪያዎች ይመልከቱ።

- ነዋሪዎች-ኤሌክትሮኒክስዎትን እንዴት መልሰው ጥቅም ላይ እንደሚያውሉ ይወቁ።
- አምራቾች- ስለአምራች ምዝገባ እና የመሰብሰብ መስፈርቶች ይወቁ።
- ቸርቻሪዎች- ስለቸርቻሪዎች ሃላፊነት ይወቁ።
- ቸርቻሪዎች- ከ eCYCLE DC ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶችን ይፈልጉ።

**በዚህ ፕሮግራም የተሸፈኑ ኤሌክትሮኒክሶች ምንድን ናቸው ("የተሸፈኑ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች" ወይም የCEE)?**

- ኮምፒውተሮች (ላፕቶፖችን፣ ታብሌቶችን፣ እና ከስድስት ኢንች በላይ ስክሪን ያላቸውን የኤሌክትሮኒክስ ማንበቢያዎችን ጨምሮ)
- የኮምፒውተር መዳፊት
- ዲቪዲ ማጫወቻዎች
- DVRቾ
- የመጫወቻ ኮንሶሎች
- የቁልፍ ሰሌዳዎች
- መቆጣጠሪያዎች (ከ6 ኢንች በላይ የሆኑ ስክሪኖች)
- ማተሚያዎች
- ቲቪዎች (ከ6 ኢንች በላይ የሆኑ ስክሪኖች)
- ቪ ሲ ኤች አር
- ሌሎች እቃዎች

- እነዚህ ኤሌክትሮኒክሶች ("የተሸፈኑ የኤሌክትሮኒክ እቃዎች") ከቆሻሻ የታገዱ ናቸው። የበለጠ ያንብቡ>>

**የተሸፈነ የኤሌክትሮኒክ እቃ ለመልሶ ጥቅም ላይ ማዋል ተቀባይነት የሚኖረው በ፦**

1. **የeCYCLE ስብስብ ዝግጅቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል**
   - እነዚህ ዝግጅቶች በኤሌክትሮኒክስ አምራቾች በከተማው ውስጥ ባሉ ቦታዎች ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን ለመሰብሰብ ይዘጋጃሉ እናም በDOEE ቁጥጥር ይደረግባቸዋል።
   - እነዚህ ዝግጅቶች የሚቀበሉት የተሸፈኑ የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን *ብቻ* ነው።
2. **የህዝብ ስራዎች መምሪያ የ Benning Road Transfer Station የኤሌክትሮኒክስ መጣል**
   - የBenning Road Transfer Station አድራሻ 3200 Benning Rd NE ነው። የኤሌክትሮኒክስ ስብስቡ የሚገኘው ሁልጊዜ ቅዳሜ ከጠዋቱ 7 ሰአት - ማታ 2 ሰአት (ከበአል ቀናት በስተቀር) እና ሁልጊዜ ሃሙስ ከወሩ መጀመሪያ ቅዳሜ በፊት ከጠዋቱ 10 ሰአት እስከ ምሽቱ 2 ሰአት (ከበአል ቀናት በስተቀር) ነው። ይህ ቦታ በኦክቶበር 2021 መጀመሪያ ላይ የተጀመረ ነው።
   - እዚህ ላይ እንደሚታየው ይህ ቦታ ከተሸፈኑ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች *የበለጠ* ይቀበላል።

"ምን ወደየት ይሄዳል" ከሚለው መሳሪያ በ eCYCLE ፕሮግራም ውስጥ *የማይካተቱትን* በዜሮ ብክነት DC ድህረ ገጽ ላይ ኤሌትሮኒክስ እንዴት በትክክል እንደሚጣል ይወቁ። የበለጠ ያንብቡ >>

ለመረጃ ደህንነት ስጋቶች፣ እባክዎ ለመረጃ-መያዣ ኤሌክትሮኒክ እቃዎች የተሻሉ ልምምዶች የሚከተሉትን ይመልከቱ። የኤሌክትሮኒክስ ሰብሳቢዎች ተጠቃሚዎች ከመልሶ ጥቅም ላይ መዋል አስቀድመው መረጃ ከመሳሪያው ላይ መወገዱን ለማረጋገጥ በገበያ ላይ የሚገኘውን መረጃ-የሚሰርዝ ሶፍትዌር እንዲጠቀሙ ይመክራሉ። የኤሌክትሮኒክ መልሶ ጥቅም ላይ ማዋያ ፕሮቶኮል መረጃ-የያዙ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን የሚሰረዝ ወይም በአካል የሚያጠፋ ነው፣ ነገር ግን ነዋሪዎች ጥብቅ ጥንቃቄ በማድረግ መረጃን መሰረዛቸው ማስተዋል ነው።

**ለተሸፈኑ ኤሌክትሮኒክሶች መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል የ2022 eCYCLE ስብስብስ ዝግጅቶች***

እነዚህ ዝግጅቶች ላይ የተሸፈኑ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች (ቴሌቪዥኖች፣ ኮምፒውተሮች፣ እና ሌሎች ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ እቃዎች) ብቻ ከዲስትሪክት ቤተሰቦች፣ አነስተኛ ለትርፍ ያልተቋቋሙ፣ እና አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ነጻ ሆነው ይቀበላሉ።

https://doee.dc.gov/ecycle

***ተጨማሪ ዝግጅቶች በቅርቡ ይለጠፋሉ**

- **ተጨማሪ የ eCYCLE DC ዝግጅቶች ሲለጠፉ ወይም ከዚህ በላይ ባሉት የክስተት ዝርዝሮች ላይ ለውጦች ካሉ ማስታወቂያ እንዲደርስዎት ይፈልጋሉ?** ማስጠንቀቂያዎችን ለማግኘት ለመጀመር፣ እባክዎ ከ "ወደ ዝርዝር አክል" የሚል ርዕስ ጋር እና የሚኖሩበትን ዋርድ ቁጥር ያካተተ ኢሜይል በproductstewardship@dc.gov ይላኩ።

በ2022፣ በእያንዳንዱ ሩብ አመት በእያንዳንዱ ዋርድ ሁለት የ eCYCLE ስብስብ ዝግጅቶች ይኖራል።

**እኛን ሊያገኙን ይችላሉ፦** እባክዎ ጥያቄዎች ካለዎ: ለproductstewardship@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ።

**ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች**:
ዘላቂ የሆኑ ቁሳቁሶች አስተዳደር
ቆሻሻዎችን እና ጎጂ ነገሮችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል
**ቆሻሻዎችን እና ጎጂ ነገሮችን መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል - ለቢዝነሶች**
DPW መልሶ ጥቅም ላይ ማዋል እና የብስባሽ ዝርዝር